# በኳታር ስራ መቀየር

## አስፈላጊ መረጃ ለሰራተኞች

ሁሉም በኳታር የሚገኙ ሰራተኞች በስራ ውላቸው ወቅት በማንኛውንም ጊዜ ካለ ምንም ተቃውሞ ሰርቲፊኬት( NOC) ሁሉም ስራዎች መቀየር ይቻላል፡፡

የ NOC ሽፋን ከሁሉም ሰራተኞች ሲነሳ ህጎቹ የስራ ውሉን የሚያቋርጡ ይሆናል፤ እንዲሁም ለተለያዩ የሰራተኛ ምድቦች ስራ ይቀየራሉ፡፡

**በቁጥር 14፣ 2014 የሰራተኛ ህግ ስር በግል ዘርፍ የሚሰሩ ከሆነ**

## ስራዎችን ለመቀየር ማድረግ ያለብኝ ምንድ ነው?

1. ስራ ለመቀየር ወደ ስራ ሚኒስቴር (MoL) ኤሌክትሮኒክ ኖኒቲፊኬሽን ሴስተም ማምልከቻ ማስገባት አለብዎት፡፡ ወደ በ"Change Employer" መግባት የቅጽ ቅጂ ፕሪንት ያድርጉ፡፡ በቅጹ እርስዎንና አሰሪዎን የሚመለከቱ መረጃዎች ሞልተው ይፈርሙ፡፡ አሰሪዎ ይፋዊ የኩባንያ ማህተም እንዲያደርግበትም ይጠይቁት፤ እንዲፈርምም ያድርጉ፡፡
2. የተሞላውንና ፊርማ ያረፈበት ቅጽ ፊቶ አንስተው ወይም ስካን አድርገው የኳታር መለያ(QID) ቁጥር እና የተንቀሳቃሽ ስልክ ቁጥር በመጠቀም ወደ MoL ኤሌክቴሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም (MoL's electronic notification system) ይግቡ፡፡ ያስታውሱ ለመግባት የሚጠቀሙበት የስልክ ቁጥር ከ QID ጋር የተያያዘ መሆን አለበት፡፡ ወደ ሲስተሙ ከገቡ በሃላ የተሞላውንና ፊርማ ያረፈበት"Change Employer" ቅጽ ይጫኑ፡፡
3. ማመልከቻውን ካስገቡ በኃላ ሲስተሙ EC(የአሰሪ ለውጥ) የሚሰጥዎት ሲሆን ይህ ብስክሪኑ ይታያል፡፡ የ EC ቁጥር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ መጻፍዎንና በስልክዎ ፎቶ ማንሳትዎን አይርሱ፡፡
4. ማመልከቻዎን በሚኒስቴር የጸደቁ ስራዎች በሚቀይርበት ወቅት የስራዎትን ለውጥ የሚገልጽ አጭር የጽሁፍ መልዕክት( SMS) ና የማሳወቅያ ጊዜ ይደርስዎታል፡፡ የአሁኑ እና አዲሱ አሰሪዎችዎም አጭር የጽሁፍ መልዕክት( SMS) ይደርሰዎታል፡፡
    - አሁን ላለው አሰሪ 2 ዓመት ወይም ያነሰ ከሰራ የማሳወቅያያ ጊዜዎ**1 ወር** ይሆናል፡፡
    - አሁን ካለው አሰሪ ከ2ዓመት በላይ ከሰራ የማሳወቅያጊዜዎ**2 ወር** ይሆናል፡፡

    የማስተዋቅያ መጨረሻ ጊዜ በሚኒስቴሩ በአጭር የጽሁፍ መልዕክቱ ተመላክቷል፡ በማስተዋቅያ ጊዜው ወቅት ከአሁኑ አሰሪው መስራት መቀጠል አለብዎት፡፡
5. ከማስተዋቅያ መጨረሻ ጊዜዎ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ አዲሱ አሰሪዎ የስራ ውልዎን የሚመለከት ዝርዝር በ አሰሪ በ MoL ዲጂታል አውቶንኬሽን ለዘርፈ ብዙ-የቋንቋ ስራ ውል(Digital Authentication System for a Multi-lingual Employment Contract) በኩል ይሰጣል፡፡ ይህ ደግሞ እርስዎንና አሰሪዎን የሚፈሩሙበት አዲስ የስራ ውል እንዲሰጥዎት ያደርጋል፡፡ ሁለታችሁም ከፈረማችሁ በኃላ አዲሱ አሰሪ እንዲጸድቅ በ MoL ዲጂታል ፕላትፎርም( MoL's digital platform )ይጭነዋል፡፡ አዲሱ አሰሪዎ በ MoL የጸደቀው ውል ሊሰጥህ ይገባል፡፡ ከ MoL ድረገጽ(MoL's website)ማውረድም ይችላሉ፡፡
6. በመጨረሻምአዲሱ አሰሪዎ አዲስ የ QID ለማግኘት ወደ ሀገር ውስጥ ሚኒስቴር የ Metrash አገልግሎት ድረ ገጽ የሚገባ ይሆናል፡፡ አዲሱ አሰሪዎ QID የሚሰጥዎት ይሆናል፡፡

## በሙከራ ወቅት ስራ ለመቀየር ተመሳሳይ ሂደት መከተል አለበኝ?

ከአሰሪዎ ጋር በመስማማት የሙከራ ጊዜ እንደሚኖርዎት በስራ ውሉ ቃሉ ተገብተልዎት ሊሆን ይችላል። ግና የሙከራ ጊዜው ስራ ከጀመሩበት ጀምሮ ከስድስት ወራት የማይበልጥ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ ከአንድ ቀጣሪ በላይ የሙከራ ጊዜ ሊኖርዎት አይችልም።

በሙከራ ወቅት ሚከተሉትን በማሟላት የስራ ውልዎን ማቋራጥ ይችላሉ:

- ስራዎን ለመቀየር ከላይ እንደተገለጸው ስራ ከመልቀቅዎ ቢያንስ አንድ ወር አስቀድሞ በ M oL ኤሌክቱሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም (MoL's electronic notification system) ማመልከቻዎን ያስገቡ።
- አዲሱ አሰሪ የአሁን አሰሪ ድርሻ የቅጥር ክፍያ ማካካስ የሚገባው ሲሆን የአሁንና አዲሱ አሰሪ በተስማሙበት መሰረት የአንድ ጊዜ የአየር ትኬት ሲሆን ክፍያው አሁን ካልዎት የሁለት ወር መሰረታዊ ክፍያ መብለጥ የለበትም።
- ሚኒስቴሩ የስራ ለውጡን ሲያጸድቅ የስራ ለውጡንና የማስተዋቅያ ጊዜውን የሚያረጋገጥ አጭር የጽሁፍ መልዕክት ከ MoL ይደርስዎታል። የማስተዋቅያ ወቅት የመጨረሻ ገዚ በአጭር የጽሁፍ መልዕክት ተመልክቷል። ከአሁኑ አሰሪዎ መስማማት ካልተፈጠረ በስተቀር ከአሁኑ አሰሪዎ ጋር ሲሰሩ ይቆየሉ።

## ለ MoL's ያስገባሁት ማመልከቻ የደረሰበትን ደረጃ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ስራ ለመቀየር በM oL ኤሌክቴሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም (MoL's electronic notification system) ማመልከቻ ካስገቡ በኃላ የደረሰበትን ደረጃ በሚከለተው ሊንክ መከታተል ይችላሉ: http://ecai.adlsa.gov.qa/
ለመግባት ማመልከቻ ባስገቡበት ወቅት የተሰጥዎትን የ QID ቁጥርዎንና እና የ EC ቁጥርን በ MoL's ኤሌክትሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም ማከተት አለብዎት።

## የማስተዋቅያ ጊዜዬን ከአሁኑ አሰሪዬን ካልጨረስኩ ምን ያጋጥማል?

ከማስተዋቅያ ጊዜው ቀደም ብለው ስራ መስራት ላለመስራት ከወሰኑ በማስተዋቅያ ጊዜው ላልሰሩበት እያንዳንዷቀን ለአሁኑ አሰሪዎ መክፈልአለብዎት።

ይህ በማስታወቅያ ጊዜው ከሚቀረብዎት ክፍያ መሰረታዊ ደሞዝ ተመሳሳይ ሲሆንበ pro rata ተመሰርቶ የሚሰላ ነው።
ለምሳሌ: ከማሳወቅያ ጊዜ ሁለት ሳምንት ቀደም ብለው ስራ ማቆም ቢፈልጉ እና መነሻ ደሞዝዎ በወር QAR 1,500 ቢሆን የስራ ውልዎ ብህጋዊ አገባብ ለማቋረጥ ለአሰሪዎ QAR 750 መክፈል ይኖርብዎታል።

## የማሳወቅያ ጊዜዬን ላለማጠናቀቅ ከአሁኑ አሰሪዬን መስማማት እችላለሁ?

አዎ፤ እርስዎንና የአሁኑ አሰሪዎ የማሳወቅያ ጊዜዎትን ላለማጠናቀቅ መስማማት ይችላሉ። እንዲህ ሲሆን እርስዎንና የአሁኑ አሰሪዎን የተስማማችሁበት ደብዳቤ ስራ ለመቀየር በሚያመለክትበት ወቅት ማያያዝ አለብዎት። ደብዳቤው ፊርማ ያረፈበት ሲሆን እርስዎንና አሰሪዎን በህግ የተቀመጠውን የማሳወቅያ ጊዜ የሚመለከት አሰራር ላለመተግበር በልዩ ሁኔታ የተስማማችሁበት ነው። MoL ስለ ማሳወቅያ ጊዜ ውሳኔ ሲሰጥ ይህ የጋራ ስምምነት ከግምት ውስጥ ያስገባዋል።

## አሰሪ በሚቀየርበት ወቅት የሚኖሩ አስተዳደራዊ ውጪዎች ማከካስ ወይመክፈል ይኖርብኛል?

አይ፤ ስራን የመቀየር ሂደት ለሰራተኞች ከክፍያ ነጻ ነው። ከዚህ በተጨማሪ QID ለማግኘት የሚወጣ ውጪ ለአዲስ አሰሪ መክፈል ወይ ማካከስ **አይኖርብዎትም።**

## ስራ ለማቀየር በማመለክትበት ወቅት የአሁኑ አሰሪዬ እኔን QID መሰረዝ ይችላልን?

ስራን ለመየቀር ማመልከቻ ወደ MoL's ኤሌክትሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም ካስገቡ በሃላ የአሁኑ አሰሪዎ እረስዎን QID ወይም ፋይል ፋልስ አብስኮንዲንግ ጉዳይ ሊሰርዝ አይችልም።

## ስራ ለመቀየር ማመልከቻ ከማስገባቴ በፊት የአሁኑ አሰሪዬን የእኔን QID ቢቀይረው ምን አደርጋለሁ ?

የአሁነ አሰሪዎ ማመልከቻ ከማስገባትዎ በፊት የQIDዎን ከሰረዘ መጀመርያ በተቀናጀ ፕላትፎርም ለቅሬታ አቅራቢዎችና መረጃ ሰጪዎች(Unified Platform for Complaints and Whistleblowers)ወይ ወደ MoL ቅሬታን ማቅረብ ይችላሉ። ሚኒስቴሩ ቅሬታዎን ከመረመረ በኃላ በአርብኛ የተጻፈ ፊርማ ያረፈበት ደብዳቤ ወደ ስራ ግንኙነት ክፍል በመጻፍ ዳግም QID እንዲሰጥዎት ይጠይቃል። በደብዳቤው ለምን QID ዳግም እንዲሰጥዎት እንደየጠየቁ በግልጽ ያብራሩ። በደብዳቤው QID እና የሞባይል ስልክ ቁጥርዎን መጥቀስዎን እርግጠኛ ይሁኑ። ፊርማ ካረፈበት የ QID ቅጂ፣ ስለ QID መሰረዝ የሚገለጽ አጭር የጽሁፍ መልዕክት ቅጂ ፤ እንዲሁም አዲስ የስራ ጥየቄ ቅጂ ማቅረብ አለብዎት። ለሪከርድ የእነዚህን ሰነዶች ቅጂ መያዝዎን አይዘንጉ።

MoL የእርስዎን QID ዳግም ለመስጠት ከሀገር ውስጥ ሚኒስቴር በጋራ ይሰራል። QIDዎን ያለበት ሁኔታ በ Metrash ማየት ይችላሉ።

Metrash ከተሰጥዎት በኃላ MoL's ኤሌክትሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም በኩል ስራ ለመቀየር ማመልከት ይችላሉ።

## ስራ የመቀየር ማመልከቻዬን መሰረዝ እችላለሁ?

ስራን ለመቀየር በM oL ኤሌክቴሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም (MoL's electronic notification system)ማመልከቻ አስገብተው ከሆነና ማመልከቻዎን እየታየ ከሆነ በሲስተሙ መሰረዝ ይችላሉ። ወደበM oL ኤሌክቴሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም (MoL's electronic notification system)የቁጥርና የሞባይል ስልክ ቁጥር በመጠቀም ይግቡ።

ከሚኒስቴሩ ማረጋገጫ የስራ ለውጥ ማመልከቻውን መቀየር ከፈለጉና ይህ ደግሞየስራ ወልዎን ማረጋገጫ ከማግኘትዎ በፊት ከሆነ የጽሁፍ ጥያቄ ለ MoL.ማቅረብ አለብዎት። ማመልከቻዎን ለመሰረዝ ፊርማዎትን ያረፈበት በአረብኛ የተጻፈ ደብዳቤ ለስራ ግንኙነት ክፍል ማቅረብ አለብዎት። በደብዳቤው ማመልከቻውን የሚሰርዙበት ምክንያት አጭር ማብራርያከ EC ቁጥር፣ የ QID ቅጂና የሞባይል ስልክ ቁጥርዎን ማካተት አለብዎት።

## አሰሪ ስቀይር የአገልግሎት መቋጫ ጥቅሞች ማግኘት እችላለሁን?

ቢያንስ አንድ ዓመት የስራ ጊዜ ካሳለፉ እና አሰሪ መቀየር ከፈለጉ ከአሁን አሰሪዎ ስራ መቋጫ አገልግሎቶች ከማምኛውንም የኣመት ዕረፍትና እና በስራ ውሉ የተጠቀሱ ሌሎች ጥቅሞች ማግኘት አለብዎት።

## ፍያዎቼን ያልተቀበልኩ ከሆነ ስራ ከማቆሜ በፊት ማሳወቅያ መስጠት አለብኝ?

የአሁኑ አሰሪዎ ህጋዊ ግዴታዎቹን(የደሞዝ ክፍያዎችን ጨምሮ) ካልተወጣ በተሻሻለው የሰራተኛ ህግ አንቀጽ 51 መሰረት አስቀድመው ሳያሳውቁ መልቀቅ ይችላሉ። ለ MoL. ሰራተኛ ግንኙነት ክፍል አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። ይህንን በተቀናጀ ፕላትፎርም ለቅሬታ አቅራቢዎችና መረጃ ሰጪዎች(Unified Platform for Complaints and Whistleblowers) ማድረግ ይችላሉ።

ያስታውሱ፣ የአገልግሎት መቋጫ ክፍያ(ከአንድ ዓመት አገልግሎት በኃላ) ደሞዎዝዎን pro rata የዓመት ዕረፍት የማግኘት መብት እንዳልዎት ያስታውሱ። ከኳታር መውጣት ቢፈልጉ አሰሪዎ የአየር ትኬት ውጪን የመሸፈን ግዴታ አለበት።

## ኳታርን ለቅቄ ከሄድኩ በኃላ ተመልሼ ስራን መያዝ እችላለሁን?

ሳያሳውቁ ወይ የማሳወቅያ ጊዜ ሳያጠናቅቁ ኳተርን ለቀው ከሄዱ በኳታር ለአንድ ዓመት ወደ ስራ መመለስ አይችሉም። እንዲሕ ዓይነት ለማስወገድ የሚከተሉትን ተግባራት ይፈጽሙ:

በሙከራ ጊዜ ኳታርን ለቀው መሄድ ከፈለጉ:

- አሰሪዎን በM oL ኤሌክቴሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም (MoL's electronic notification system)ማሳወቅ አለብዎት። የማሳወቅያ ጊዜ ከአሰሪዎ ጋር መስማማት ያለብዎት ሲሆን ከሁለት ወር ግን መብለጥ የለብዎትም።
- የማሳወቅያ ጊዘየዎትን ሳያጠናቅቁ መልቀቅ ከፈለጉ የሚቀረውን የማሳወቅያ ጊዜ የመነሻ ደሞዝ ለአሰሪዎ መክፈል አለብዎት፤ መጠኑ የሁለት ወር የመነሻ ደሞዝ መብለጥ የለበትም።

ከሙከራ ጊዜ በኃላ ኳታርን መልቀቅ ቢፈልጉ:

- ከአሰሪዎ ለሁለት ዓመት ወይ ያነሰ ከሰሩ የስራ ውሉን ከመቋረጡ አንድ ወር አስቀድመው በM oL ኤሌክቴሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም (MoL's electronic notification system)ማሳወቅ አለብዎትን።
- ከአሰሪዎ ከሁለት ዓመት በላይ ከሰሩ የስራ ውሉን ከመቋረጡ ሁለት ወር አስቀድመው በM oL ኤሌክቴሮኒክ ኖቲፊኬሽን ሲስተም (MoL's electronic notification system)ማሳወቅ አለብዎትን።
- ከላይ የተጠቀሰውን የማሳወቅያ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ኳታርን መልቀቅ ከፈለጉ ለሚቀረውን የማሳወቅያ ጊዜ የመነሻ ደሞዝ መጠን ያለው ካሳ ለአሰሪው መክፈል አለብዎት።

## አሰሪዬ ስራ ውን ማቋረጥ ይችላልን?

አዎ፤ አሰሪዎ የስራ ውልዎን ሊያቋርጥ ይችላል።

1. በሙከራ ጊዜ አሰሪዎ "ኃላፊነትዎን ለመወጣት ብቃት አንሶት ሲያገኝዎት" በስራ ውልቆ ላይ እንደተገለጸው አሰሪዎ ውሉን ማቋረጥ ይችላል፤ ነገር ግን ስራውን ከመቋረጡ በፊት አንድ ወር ቀደም ብሎ በ MoL's ኤሌክትሮኒክ ሲስተም ሊያሳውቅዎት ይገባል።

   ስራ በሚቋረጥበት ወቅት እርስዎ ወደሚኖሩበት ሀገር ለመመለስ ቢፈልጌ አሰሪው የመመለሻ የአየር ትኬት ወጪን መሸፈን አለበት።

2. ከሙከራ ጊዜ በኃላ አሰሪዎ የስራ ውሉን ማቋረጥ ከፈለገ በበኤሌክትሮኒክ ሲስተሙ ሊያሳውቅዎት ይገባል።
   - ከአሰሪዎ ለሁለት ዓመት ወይ ያነሰ ከሰሩ የማሳወቅያ ጊዜው አንድ ወር ነው።
   - ከአሰሪዎ ከሁለት ዓመት በላይ ከሰሩ የማሳወቅያ ጊዜው ሁለት ወር ነው።

እርስዎንና አሰሪዎን በማሳወቅያ ጊዜ ደንብና ሁኔታዎችን ማክበር አለባችሁ።

## አሰሪዬ የማሳወቅያ ጊዜውን ሳያከብር እኔን ማሰናበት ይችላልን?

አሰሪዎ የማስታወቅያ ጊዜውን ሳያከብር የስራ ውሉን ካቋረጠ በቀሪው የማሳወቅያ ጊዜ መነሻ ደሞዝዎን የሚሸፍን የካሳ ክፍያ መክፈል አለበት

ለምሳሌ፡ መነሻ ደሞዝዎ በወር QAR 1,500 ቢሆንና አሰሪዎ ከአንድ ወሩ የማሳወቅያ ጊዜ ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ ስራ እንዲያቆሙ ቢያደርግዎት የስራ ውልዎ ብህጋዊ አገባብ ለማቋረጥአሰሪዎ QAR 750 ሊከፍልዎት ይገባል።

## ስራ በሚቋረጥበት ወቅት ወደ ምንኖርበት ሀገር የመመለሻ የበረራ ትኬት አሰሪዬን መክፈል ይኖርበታል?

አሰሪዎ የስራ ውሉን ከተቋረጠበት ቢበዛ በሁለት ሳምንት ወደ ሚኖሩበት ሀገር የሚመለሱበት የትኬት ወጪን ጨምሮ የመመለሻ አሰራሮችን ማክበር አለበት። ሀገሪቱን ከመልቀቅዎ በፊት ወደ ሌላ አሰሪ ከተቀጡ የመመለሻ ግዴታን የሚመለከት የአዲሱ አሰሪ ይሆናል።

ውሉን አቋርጠው ኳታርን ለቀው የመሄድ ዕቅድ ሲኖርዎት የማሳወቅያ ጊዜ አክብረው(ከተሻሻለው የሰራተኛ ህግ አንቀጽ 51 መሰረት ውጭ) አሰሪዎ እርስዎ ከሙሉ የስራ ውሉ ካጠናቀቁት የስራ ቆይታ አንጻር ታይቶ ተመጣጣኝ የአየር ትኬት ወጪን ይከፍላል። ለምሳሌ፤ የሁለት ዓመት የስራ ውልዎን አንድ ዓመት ከሰሩ በኃላ ካቋረጡ አሰሪዎ ከመመለሻ ትኩት ወጪዎን ግማሹን ይሸፍናል።

## በልዩ ህጎች ለታቀፉ ሰራተኞች

## የቤት ሰራተኞች ስራ ለማቋረጥና እና ለመቀየር የሚያገለግሉ ህጎች የተኞቹ ናቸው?

የቤት ሰራተኞች ስራ ለማቋረጥና ለመቀየር ስራ ላይ የሚውሉ ህጎች በሰራተኛ ህግ ቁጥር 14፣ 2004 ከታቀፉ የግል ሰራተኞች ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህን የሚመለከት የቤት ሰራተኞችን የተሻሻለ ስታንዳርድ የስራ ውል ተዘጋግቷል። ነገር ግን የቤት ሰራተኞች የሙከራ ጊዜ ከ3 ወራት መብለጥ የለበትም። ከዚህ በተጨማሪ የቤት ሰራተኛ በተመሳሳይ ጊዜ በአንድ አሰሪ ብቻ የሙከራ ጊዜ የሚኖረው።

ሰራተኛው በስራ ውሉ ወይ በበቤት ሰራተኞች ህግ አንቀጽ11 እና 16  ቁጥር  15 ፣2017  የተጠቀሱን ክፈጸሙ አሰሪዎች ሳያሳውቁ በግላቸው ከስራ ማባረርና እና የስራ መቋጫ ክፍያ አለመክፈል ይችላሉ።

ከዚህ በተጨማሪ በ በቤት ሰራተኞች ህግ አንቀጽ17 እና ቁጥር 15 ፣2017 በተገለጹ ጉዳዮች በስራው ውሉ ሂት ያለ ምንም ማሳወቅያ በግላቸው ውሳኔ  የስራ ውሉንሊያቋርጡ የሚችሉ ሲሆን የስራ መቋጫ ክፍያ፣ pro rata የኣመት ዕረፍት ክፍያንና ወደ ሀገሩ/ሯ መመለሻ የአየር ትኬት ውጪን ይከፍላሉ።

## የግብርና ከብት እርባታ እንዲሁም የአሳ ማጥመደ ሰራተኞች ስራ ለማቋረጥ የሚያገለግሉ ህጎች የተኞች ናቸው?

የግብርናና የከብት እርባታ እንዲሁም የአሳ አትማጅ ሰራተኞች ስራ ለማቋረጥና ለመቀየር ስራ ላይ የሚውሉ ህጎች በሰራተኛ ህግ ቁጥር 14፣ 2004 ከታቀፉ የግል ሰራተኞች ጋር ተመሳሳይ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አዋጅ 17፣ 2012 የማመልከቻ የተወሰኑ የሰራተኛ ህግ ቁጥር 14፣ 2004 በግብርናና እና ከብት እርባታ ሰራተኞች የሚመለከት ተካቷል።

## የአሁኑ አሰሪዬ ወደ ሌላ አሰሪ እንዳልሄድ እየከለከለኝ ከሆነ ወይም ተጨማሪ መረጃ ብፈልግ ምን አደርጋለሁ?

የአሁኑ አሰሪዎ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ስራ እንዳይቀይሩ እየከለከልዎት ከሆነ ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሰራተኛ ሚኒስቴር የሰራተኛ ግንኙነት ክፍል በሆትላይን (40288101)፤ ኢመይል info@mol.gov.qa ድረ ገጽ www.mol.gov.qa ወይመ ጽህፈት ቤታችንን ይጎብኙ። እንዲሁም  ቅሬታዎን በተቀናጀ ፕላትፎርም ለቅሬታ አቅራቢዎችና መረጃ ሰጪዎች(Unified Platform for Complaints and Whistleblowers) ማቅረብ ይችላሉ።